የጎንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበበ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት

የነገረ ሃይማኖት ትምህርት



አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ግንቦት ፲፪

ማውጫ

ነገረ ሃይማኖት 3

ሃይማኖትና ፍልስፍና 3

የፈጣሪን መኖር በምን እናውቃለን?..... 4

ሃይማኖትና ሳይንስ 4

ዕቅበተ እምነት 4

የሃይማኖት ጥቅም 5

ሃይማኖት በዘመናት 5

የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች 5

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር 5

ምሥጢረ ሥላሴ 5

ነገረ ሃይማኖት

ነገረ ሃይማኖት ስለ ሃይማኖት የሚናገር የቤተክርስቲያን ትምህርት ነው። ሃይማኖት ሃይመኑ-አመነ፣ አሳመነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ምዕላድ ሲሆን ትርጉሙ ማመን መታመን ማለት ነው። ማመን ማለትም የዚህች ዓለም ፈጣሪ፣ አስተዳዳሪ፣ መጋቢ አላት ብሎ ሳይጠራጠሩ በልብና ከልብ መቀበል ማለት ነው። መታመን ማለት ደግሞ ያመንነውን ነገር በአንደበት መመስከርና በተግባር ማዋል ነው። የትምህርተ ሃይማኖት መሠረቱ የፈጣሪ መኖር ነው።

ሃይማኖትና ፍልስፍና

ፍልስፍና ፈልሰፈ-ጥበብ ተናገረ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ጥበብ ማለት ነው። ጥበብን መውደድም ፍልስፍና ይባላል። ፍልስፍና ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት። እነዚህም ሐሳባዊ ፍልስፍና እና ተግባራዊ ፍልስፍና ናቸው። በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ የሚጠኑት ግኖሶሎጂ እና ሜታፊዚክስ ናቸው። በተግባራዊ ፍልስፍና ውስጥ የሚጠኑት ደግሞ ሥነ አመክንዮ (Logical reasoning)፣ ሥነ ምግባር (Ethics) እና ሥነ ውበት (Aesthetics) ናቸው። በግኖሶሎጂ የሚጠኑ ጉዳዮች፡-

- ✓ የዕውቀታችን ወሰንና ኀይል እስከምን ድረስ ነው የሚለው
- ✓ የዕውቀታችን ዋና ምንጭ ምንድን ነው የሚለው
- ✓ ዕውቀታችን የሚያርፍበት ሐሳባችን ሁሉ የሚወድቅበት የውጭ ነገር ምን እንደሆነ

የዕውቀታችን ወሰንና ኀይል እስከምን ድረስ ነው በሚለው ሥር አምስት ጉዳዮች አሉ።

1. ዶግማቲዝም
2. ስኬፕቲስዝም
3. ፕራግማቲዝም
4. ፖዝቲቪዝም
5. ክሪቲሲዝም

የዕውቀት ምንጭ ምንድን ነው በሚለው ደግሞ ሥስት እይታዎች አሉ። እነዚህም፡- ኢምፕሪሲዝም፣ ራሽናሊዝም፣ ክሪቲሲዝም ናቸው። በሜታፊዚክስ የሚጠኑ ጉዳዮች ደግሞ በዋናነት ሁለት ናቸው። እነዚህም ኦንቶሎጂና ኮዝሞሎጂ ናቸው። ኦንቶሎጂ በዚህ ዓለም ያሉ ነገሮች ከምን ተሠሩ መነሻቸው ምንድን ነው የሚለውን ያብራራል። በኦንቶሎጂ ውስጥ አራት እሳቤዎች ይጠናሉ። እነዚህም፡-

1. ማቴሪያሊዝም፡- በዓለም ያለ ነገር ሁሉ ቁሳዊ ነው
2. አይዲያሊዝም፡- በዓለም ያለ ነገር ሁሉ መንፈስ ነው
3. ፓራሌሊዝም፡- በዓለም ውስጥ ቁስም መንፈስም አለ
4. ዱያሊዝም፡- የመንፈስ ፈጣሪ ሌላ የቁስ ፈጣሪ ሌላ ነው ይላል

ኮዝሞሎጂ ዓለም ስለሚካሄድበት ሥነ ሥርዓትና ስለሕይወት አገኛኘት ይገልጻል። ዓለም ስለሚካሄድበት ሥርዓት የሚከተሉት እሳቤዎች ይጠናሉ።

1) ሜካኒዝም፡- የፈጣሪን ህልውና የሚክድ እሳቤ ነው
2) ቲሎሎጂዝም፡- ይህም የፈጣሪን ህልውና አይቀበልም

3) ኮዝሞሳኒ፡- ዓለም የተፈጠረው በእግዚአብሔር እንደሆነ ይገልጻል።

በሕይወት አገኛኘት ዙሪያ ሁለት እሳቤዎች አሉ። እነዚህም ዝግመተ ለውጥና ቲዮሎጂ ናቸው። በዝግመተ ለውጥ እሳቤ ዓለም አሁን ያለችበትን ቅርጽ ልትይዝ የቻለችው በአካባቢ ተጽእኖ (Natural selection)፣ በውርስ (Heredity) ና በሌሎች ተጽእኖዎች ነው ይላሉ። ስለእግዚአብሔር መኖርና ከዓለሙ ጋር ስላለው ግንኙነት አምስት እሳቤዎች አሉ። እነዚህም፡-

- ቴይዝም፡- ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ይላል
- ዴይዝም፡- እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ትቶታል
- ፓንቴይዝም
- ፓኔንቴይዝም፡- ይህን ዓለም የእግዚአብሔር አንድ አካል እንደሆነ የሚያስብ
- አቴይዝም፡- የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ እሳቤ ነው።

የፈጣሪን መኖር በምን እናውቃለን?

1. በመገለጥ (በሕልም፣ በራእይ፣ ቃሉን በመስማት፣ በዘፈቀደ በመገለጥ)
2. በተአምራትና በሌሎችም ድንቆች የተገለጠነውን አምኖ በመቀበል
3. በሥነ ፍጥረት
4. በሥራው
5. በመጽሐፍ ቅዱስ
6. በተአምር
7. በታሪክ
8. በሥጋዌ (በአምላክ ሰው መሆን)
9. በጸሎት

ሃይማኖትና ሳይንስ

ሳይንስ በቤተ ሙከራና በተለያዩ ምርምሮች አማካኝነት የሚገኝ ማስረጃን መሠረት ያደረገ ዕውቀት ነው። ሃይማኖት እግዚአብሔርን በማመን ፍጥረታትን ተመራምሮ ለሰው ልጅ አገልግሎት ለማዋል የሚደረገውን ሳይንሳዊ ምርምር አይቃወምም። ሳይንስ እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ ተጠቅመን የሚገኝ ዕውቀት ነው። ስለዚህም ሳይንስ ስላሉ ፍጥረታት ይናገራል እንጂ ከመጀመሪያው ፍጥረታትን እንዲኖሩ ያደረጋቸው ማን ነው ለሚለው በቂ ምላሽ የለውም። የሳይንስ ቋሚ እውነት የለውም። ለሃይማኖት ግን ቋሚ እውነት አለው። በዓለም ላይ ሦስት ዓይነት አማኞች አሉ። እነዚህም፡-

- በትክክለኛ ሃይማኖት ያሉ (ኤፌ.4፥5
- በተሳሳተ እምነት ያሉ (ኤር.17፥5)
- ምንም እምነት የሌላቸው (መዝ.13፥1)

የብዙ እምነቶች መፈጠር አንዱ ምክንያት የተጻፈውን ከዐውድ በመለየት የራስን የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት ነው።

ዕቅበተ እምነት

ዕቅበተ እምነት ማለት ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን እውነት ተቀብሎ መጠበቅና ለትውልድ ማስተላለፍ ማለት ነው። የዕቅበተ እምነት ዋና ዓላማ ምእመናን ትክክለኛውን ሃይማኖት አውቀው ከሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው።

የሃይማኖት ጥቅም

- ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ፈጣሪን ለማወቅ
- የተረጋጋ ሕይወትን ለመኖር ረድኤትን ለማግኘት
- ከየት እንደመጣንና ለምን እንደምንኖር እንዲሁም ወዴት እንደምንሄድ ለማወቅ

ሃይማኖት በዘመናት

እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ ሃይማኖትም አንዲት ናት። የዚህች የአንዲ ሃይማኖት አማኞች ግን በየዘመናቱ የተለያዩ ስያሜዎች ነበራቸው። በየዘመናቱ የተለያዩ ስያሜዎች የተሰጠው ያው አንዱ ሃይማኖት ነው እንጂ በየዘመናቱ የተመሠረተ ሃይማኖት ኖሮ አይደለም። አማኝ፣ አይሁድ፣ ደቀመዛሙርት፣ ክርስቲያን፣ ኦርቶዶክስ፣ ተዋሕዶ ይላሉ። አሁን አይሁድ የሚባሉት ግን ከትክክለኛው አስተምህሮ ያፈነገጡ አካላት ናቸው።

የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች

- መጽሐፍ ቅዱስ (Holy Bible) የቤተክርስቲያን አባቶች
- ቅዱስ ትውፊት (Holy Tradition)

ምንጭ ወይም መነሻ የሌለው ሐሳብ ጕስዐተ ልብ ይባላል።

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

አዕማድ ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። ምሥጢር ማለት ደግሞ ድብቅ፣ ሥውር፣ ረቂቅ ማለት ነው። አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የሚባሉት፡-

1. ምሥጢረ ሥላሴ
2. ምሥጢረ ሥጋዌ
3. ምሥጢረ ጥምቀት
4. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን
5. ምሥጢረ ቍርባን

ናቸው። እነዚህም ምሥጢር የተባሉበት ምክንያት ለሚያምን በእምነት የሚረዱ ለማያምን የተሠወሩ በመሆናቸው ነው። በተጨማሪም ከሰብኣዊ ምርምር በላይ ስለሆኑ ነው።

ምሥጢረ ሥላሴ

ቅድስት ሥላሴ ማለት ልዩ ሦስትነት ማለት ነው። ይኸውም የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሦስትነታቸው ከፍጡራን ሦስትነት የተለየ ሦስትነት በመሆኑ ነው።

አካላተ ሥላሴ

እግዚአብሔር በአካል ሦስት ሲሆን የእያንዳንዱ አካል ስም ደግሞ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው (ማቴ.28፥19)። ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳቸው ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አላቸው። ሦስቱ አካላትም በየራሳቸው ጸንተው ይኖራሉ።

ባሕርየ ሥላሴ

ባሕርይ ማለት አካላዊ ህልው አካል ማለት ነው። ይኸውም አካል ያልሆነ በአካል ግን ያለ ማለት ነው። የሦስቱ አካላት በኵነታት መገናዘብ ባሕርይ ይባላል (ሃይ.አበ.11፥9)።

ኩነታተ ሥላሴ

ከዊን ወይም ኩነት ማለት መሆን ማለት ነው። ኩነት ሲበዛ ኩነታት ይላል። የአብ የከዊን ስም ልብ ነው፣ የወልድ የከዊን ስም ቃል ነው፣ የመንፈስ ቅዱስ የከዊን ስም እስትንፋስ ነው። በኩነታት መገናዘብ እንጂ መለያየት የለም።

- አብ፡- ልብ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ ነው
- ወልድ፡- ቃል፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ ነው
- መንፈስ ቅዱስ፡- ሕይወት፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ለባዊ፣አለባዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ ነው

ግብረ ባሕርይ

ሦስቱ አካላት ማለትም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተገናዝበው በአንድነት የሚሠሩት ሥራ ግብረ ባሕርይ ይባላል (ሃይ.አበ.53፥5)። ሦስቱ በግብረ ባሕርይ አንድ ናቸው። ይኸውም በምልዐት፣ በዕውቀት፣ በማዳን፣ በርቀት፣ በዘለዓለማዊነት፣ በጎያልነት፣ በንጉሥነት፣ በባዕልነት፣ በጻድቅነት፣ በቅዱስነት፣ በታጋሽነት፣ በፈጣሪነት፣ በሁሉን ቻይነት፣ በክብር፣ በጥበብ፣ በፍቅር፣ በአምላክነት፣ በጌትነት፣ በመጋቢነት፣ በመሓሪነት፣ በፈታሒነት፣ በምስጋና፣ በአለመለወጥና በመሳሰሉ ነገሮች አንድ ናቸው ማለታችን ነው።

ግብረ ልደት (አካላዊ ግብር)

ሦስቱ አካላት በአካላዊ ግብር ይለያያሉ። የአብ ግብሩ መውለድ፣ ማሥረጽ ነው። የወልድ ግብሩ መወለድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረጽ ነው።

ስም

የሦስቱ አካላት የአካል፣ የአካላዊ ግብር፣ የግብረ ባሕርይ፣ የከዊን ስም እንደሚከተለው ነው።

የአካል ስም	የአካል ግብር ስም	የከዊን ስም	የባሕርይ ግብር ስም
አብ	ወላዲ፣ አሥራጺ	ልብ	እግዚአብሔር፣ አዶናይ፣ ኤልሻዳይ፣ ኤል ኤሎሄ፣ ጸባዖት፣ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ጌታ፣ ንጉሥ....ወዘተ
ወልድ	ተወላዲ	ቃል	
መንፈስ ቅዱስ	ሠራጺ	እስትንፋስ	

መለኮት

በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮት የሚለው ቃል በብዙ ይተረጎማል። በዋናነት መለኮት ሦስቱ አከላት አንድ ለሚሆኑበት ባሕርይ ስም ይሆናል። መለኮት መለከ-ገዛ ከሚለው ቃል ወጥቶ ጌትነት፣ ገዥነት ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። እያንዳንዱ የአካል ከዊን መለኮት ሲባል የሚገኝበት ጊዜም አለ።